# ምድር ብታወራ

ምድር ስንቱን ቻለች ፣ ስንት አለ በውስጧ
ጩኸቷ አረመኔ ፣ ችላ መቀመጧ
ስንት ንብረት ጠፋ ፣ ስንቱ ተሰረቀ ?
ስንት ፍርድ ተዛባ ፣ ስንት በግፍ ታነቀ ?
ምድር አትናገር ፣ አፍም አልተገኘ
ጠያቂ ቢጠፋ ፣ ግፍ ባገር ላይ ናኘ ።

አላግባብ በምድር ፣ ስንት ደም ፈሰሰ ?
ስንት አጥንት ተሰብሮ ፣ ስንት ተከሰከሰ ?
ስንቱ ተማረረ ፣ ስንቱስ አለቀሰ ?
ማን ተጠየቀበት ፣ ማንስ ተከሰሰ ?

ተስፋ ተሟጦበት ፣ ህዝብ ቅስሙ ተሰብሮ
አገር ሲያል ሆኖ ፣ መውጫው ተቀርቅሮ
ሰው መሄጃው ጨንቆት ፣ ሲናወጥ ሲሸበር
ዜጋ እንደ ፍሪዳ ፣ ሲበለት ሲመተር
መቶ ሁለት መቶ ፣ በጅምላ ሲቀበር
ምድር ብታወራ ፣ ምን ትነግረን ነበር ?
ምን ታዝባ ይሆን ፣ ከዓይን የተሰወረ ?
ሰው ከነ ህይወቱ ... ገደል የተጣለ ፣ የተወረወረ?
ወይንስ ሌላም አለ ... ለህሊና ዘግናኝ ፣ ከዚህ የመረረ?

እኮ ምን ትላለች ...
ምድር ብታወራ ፣ ያየችውን ሁሉ
የግፍ የጭካኔ ፣ ያልቃል ወይ ገድሉ ?
ሰው እንደ ዳመና ፣ እንደ ጢስ ሲጠፋ
እንደ ቁርበት ሲታሽ ፣ ሲረገጥ ሲለፋ
ቀን ሲጨልምበት ፣ ስትርቀው ተስፋ
ዜጋ የማያውቀው ፣ ተንኮል የከረፋ
ምን ትነግረን ይሆን ፣ ከዚህ የሚከፋ ?

በጨካኞች ቀንበር ፣ በሰንሰለት ታስሮ
ሰው ከነ ህይወቱ ፣ እጉድጓድ ተቀብሮ
በምድራዊ ሲያል ፣ ሲኖር ተወርውሮ
ስንት ግፍ በሰማን ፣ የሚቀፍ ለጆሮ
ለብዙ ዘመናት ፣ ያለ ተሰውሮ
ስንቱን ባወጋችን ፣ የሰቆቃ ኑሮ
ምድር ብትናገር ፣ አፍ ቢኖራት ኖሮ ።

ምነው አፍ በኖራት ፣ ምድር ባወራችው
የተደበቀውን ፣ ሚስጥር ባወጣችው
በዝምታ ይዛ ፣ ስንቱን ጉድ ቻለችው
እንደምን አስችሏት ፣ አስተናገደችው ።

ታዛቢው ... March 13, 2012